በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.240463

ጥቅምት 01/2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሔለን ጌታቸው፤ የህፃን የማርያም አበራ ሞግዚት -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ አዳም አበራ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የአባትነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/293688 ላይ ጥቅምት 17/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀናበትን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ በጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመቃወም ተጠሪ ነበሩ፡፡ የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከት የአሁን አመልካች ተጠሪ ሟች አቶ አበራ ብርሃኑ አባቱ ስለመሆኑ ያወጣውን የአባትነት ማስረጃን በመቃወም ሟች ባለቤታቸው ሞግዚት ለሆኑላት ህፃን ወላጅ ከመሆናቸው ውጪ ሌላ ልጅ የሌላቸው በመሆኑ ለተጠሪው ሟች አባቱ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስለመሆኑ ተገልፆ የተሰጣቸው የአባትነት ማስረጃ ይሻርልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሟች ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ወርቅነሽ ይመር ጋር በነበራቸው ከጋብቻ ውጪ ግኑኝነት በ1987 ዓ.ም የወለዷቸው መሆኑን እና በሟች ወላጆች ቤት በሟች ወላጅ አባት ስም ሲጠሩ የቆዩ መሆኑን እና ሟችም የትምህርት ወጪያቸውን እየሸፈኑ ያስተምሯቸው እንደነበረ፤ ሟች በሞተበት ወቅትም ከመቃወም አመልካች የተወለደችውን ህፃን ጨምሮ ሁለት ልጅ ያላቸው መሆኑ በህይወት ታሪካቸው ላይ መነበቡን እና የመቃወም አመልካችም ይህን እንደሚያውቁ በመግለፅ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሟች አቶ አበራ ብርሃኑ ልጅ ናቸው? ወይስ አይደሉም? ቀደም ሲል ተጠሪ የሟቹ ልጅ ናቸው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሊሻር ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኙን ምስክር ሰምቷል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርናሽናል ክሊኒካል ላቦራቶሪ ከሟች አስክሬን እና ከተጠሪ ላይ ናሙና ወስዶ የዘረመል ምርመራ በማድረግ ውጤቱ እንዲገልፅለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ አግባብ የምርመራ ውጤቱ የቀረበ ቢሆንም ከሟች ላይ የተወሰደው ናሙና በንክኪ እና አከባቢያዊ ብክለት ምክንያት ተገቢውን ውጤት ሊሰጥ አልቻለም የሚል ውጤት በመገለፁ በድጋሚ አመልካች ሞግዚት ከሆኑላት ህፃን ላይ ናሙና ተወስዶ ምርመራ እንዲከናወን ታዟል፡፡ በድጋሚ በመጣው ውጤትም በአንድ ወላጅ ከሚገናኙ ወንድማማቾች/እህትማማቾች ጋር ሲነፃፀር ተጠሪ እና አመልካች ሞግዚት የሆኑላት ህፃን መካከል ግኑኝነት አለመኖሩ 192 እጥፍ መሆኑን እና ውጤቱ በአንድ ወላጅ ብቻ የሚገናኙ ወንድማማቾች/እህትማማቾች ናቸው የሚለውን ማጠቃለያ አይደግፍም በሚል ተገልጿል፡፡

ፍርድ ቤቱም ምርመራውን ያከናወነው ተቋም ልዩ አዋቂ ባለሙያ ልኮ በቀረበው የምርመራ ውጤት ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት አዝዟል፡፡ ሆኖም ተቋሙ ለምርመራ የሚወሰደውን ናሙና አሜሪካን ሀገር ልኮ እያስመረምረ ውጤቱን ከሚገልፅ በቀር በተጠየቀው አግባብ ሙያዊ ማብራሪያ ሊሰጥ የሚችል ባለሙያ እንደሌለው በመግለፁ ከፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት የዘረመል ምርመራ ባለሙያ ቀርቦ ውጤቱ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ከዳይሬክቶሬቱ የቀረቡት ባለሙያም የዘረመል ምርመራ ውጤቱ በተጠሪ እና አመልካች ሞግዚት በሚሆኑላት ህፃን መካከል ያለው የዝምድና መጠን 25% በመሆኑ ተጠሪ የሟች ልጅ አይደለም ተብሎ መደምደም እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ይህንን እና በግራ ቀኙ ምስክሮች የተነገረውን ፍሬ ነገር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ሟች አቶ አበራ ብርሃኑ የአሁን ተጠሪን ስለመውለዱ አልሰማንም፤ አልነገረንም ከማለት በቀር ሟች የአሁን ተጠሪን ያልወለዱ ስለመሆኑ አላስረዱም፤ በአንፃሩ የአሁን ተጠሪ ከሟች አቶ አበራ ብርሃኑ እና ወ/ሮ ወርቅነሽ ይመር መወለዳቸውን፤ ሟች ተጠሪን ወስደው ወላጅ እናቱ ዘንድ እንዲያድግ በማድረግ ለአስተዳደጉ አስፈላጊ የሆኑትን እገዛ እና እንክብካቤ ሲያደርጉለት የነበረ ለመሆኑ ባሰማቸው የሰው ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ያስረዳ መሆኑን፤ የዘረመል ምርምራ ውጤቱም በግልፅ የአሁኑ ተጠሪ ከሟች አልተወለደም የሚያስብል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይደለም በማለት በአሁን አመልካች በኩል የቀረበውን መከራከሪያ ውድቅ አድርጎ ቀደም ሲል ተጠሪ የሟች አቶ አበራ ብርሃኑ ልጅ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሊሻር አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአሁን የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 09/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት በዘረመል ምርመራ ውጤቱ ላይ ተጨማሪ የባለሙያ አስተያየት የመሰማቱን እና እርሱን ተከትሎ የደረሰበት መደምደሚያ አግባብነት በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካች መከራከሪያ ይዘት የስር ፍርድ ቤት በዘረመል ምርመራ ውጤቱ ላይ ተጨማሪ የባለሙያ ምስክር አስቀርቦ መስማቱም ሆነ የባለሙያውን አስተያየት የተረዳበት መንገድ እንዲሁም የዘረመል ምርመራ ውጤቱ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን የተጠሪ መከራከሪያ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የቀረበውን የምርመራ ውጤት እና የምስክሮች ቃል መሰረት ያደረገ በመሆኑ ጉድለት የለበትም የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አባትነት በፍርድ ሊረጋገጥ የሚችለው ልጅ በተፀነሰ ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመደፈር ወይንም የመጠለፍ ተግባር ተፈፅሞባት የሆነ እንደሆነ፣ ሆነ ተብሎ በእናቲቱ ላይ የማሳሳት ተግባር ተፈፅሞ የሆነ እንደሆነ፣ አባት በተባለው ሰው የተፃፉ እና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይንም ፅሁፎች ሲገኙ፣ በህግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖርም የእናቲቱ እና አባት የተባለው ሰው መካከል የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲኖር አልያም የልጅ አባት የተባለው ሰው ለልጁ እንደ አባት የመንከባከብ ተግባር ይወጣ እንደነበር ሲረጋገጥ መሆኑን ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 143 ከ(ሀ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች ያስገነዝባሉ፡፡ ይሁን እንጂ የቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 144 (ሀ) (ሐ) በህክምና ወይንም በደም ምርመራ እናትየው በወቅቱ የግብረ ስጋ ግንኙነት የነበራት አባት ከተባለው ሰው ጋር አለመሆኑ ሲረጋገጥ ወይንም አባት የተባለው ሰው በእርግጥም አባት አለመሆኑ ሲረጋገጥ ከላይ በተገለፀው አግባብ አባትነትን በፍርድ ማረጋገጥ እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል የዘረመል ምርመራ አባትነትን በሌላ ማስረጃ ከማስረዳት የማይከለክል እና የምርመራ ውጤቱም ብቻውን ገገር እንዳልሆነ ይኸው ችሎት በመ/ቁ/90121፣ 148570 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አንድን ጉዳይ ለማብራራት ልዩ አዋቂ ባስፈለገበት ጊዜም ፍርድ ቤቶች የልዩ አዋቂውን አስተያየት መስማት የሚገባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 136 ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ሟች አቶ አበራ ብርሃኑ ከተጠሪ ወላጅ እናት ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የነበረው መሆኑ እና ሟች ለተጠሪ እንደ አባት እንክብካቤ ያደርግለት የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ አስቀርቦ ባሰማቸው የሰው ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ያስረዳ ስለመሆኑ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የዘረመል ምርመራ ውጤቱን በተመለከተ ደግሞ ቀድሞ ከሟች አስክሬን ላይ የተወሰደው ምርመራ በንክኪ እና አከባቢ ብክለት ምክንያት ተገቢውን ውጤት መስጠት አይችልም ስለተባለ በዚህ ረገድ አስተማማኝ የዘረመል ምርመራ ውጤት ቀርቧል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ሞግዚት ከሆኗት ህፃን ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተወሰደው ናሙና ተጠሪ የሚች ልጅ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ያለውን አስረጂነት በተመለከተ በፅሁፍ የቀረበው ውጤት ግልፅ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ የባለሙያ አስተያየት መስማቱም የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቱ በቀረበው የዘረመል ምርመራ ውጤት ላይ የባለሙያ አስተያየት መስማቱም ሆነ ሚች የተጠሪ አባት ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ሆኖ ባለመገኘቱ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/293688 ላይ ጥቅምት 17/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

## ተጨማሪ ትዕዛዝ

ከፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበው የመ/ቁጥር 195288 መዝገብ በመጣበት አግባብ በተገቢው ጥንቃቀተ ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !